# ለ COMIRNATY (የሚነበበው Cuh-mir'-na-tee ተብሎ ነው)
# (COVID-19 ክትባት፣ mRNA)
# (2023-2024 Formula)
# ተቀባዮችና ተንከባካቢዎች የቀረበ መረጃ

ይህ ሰነድ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር የመነጋገርን ቦታ እንዲተካ ተብሎ የታሰበ አይደለም። ምንም አይነት ጥያቄ ካለዎት ወይም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይነጋገሩ።

**COMIRNATY ምንድን ነው?**
COMIRNATY ዕድሜያቸው 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች COVID-19ን ለመከላከል ጥቅም ላይ የሚውል ክትባት ነው።

የ COMIRNATY ክትባት ሁሉንም የተከተቡ ሰው ላይከላከል ይችላል።

COMIRNATY COVID-19ን የሚያመጣውን SARS-CoV-2ን አይዘም። COMIRNATY COVID-19 ሊያሲዝዎት አይችልም።

**COMIRNATY መከተብ/መውሰድ የሌለበት ማን ነው?**
በሚከተሉት ሁኔታዎች COMIRNATY መውሰድ የለብዎትም፥
- ቀደም ሲል የ COMIRNATY ወይም የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባትን ዶዝ ከወሰደ በኋላ ከባድ አለርጂ ካጋጠመው[1]
- በእነዚህ ክትባቶች በየትኛውም ግብአት ምክንያት ከባድ አለርጂ አጋጥሞ ከነበረ(**የCOMIRNATY ግብዓቶች ምንድን ናቸው?** የሚለውን ይመልከቱ)።

**COMIRNATY ከመከተብዎ በፊት ለክትባት አቅራቢዎ የሚከተሉትን ጨምሮ ስለ ሁሉም የጤና ሁኔታዎችዎ ይንገሩት:**
- የትኛውም አላርጂዎች ካሉብዎ
- ቀደም ሲል ማንኛውንም የCOVID-19 ክትባትን ዶዝ ከወሰዱ በኋላ ከባድ አለርጂ ካጋጠመዎ
- ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት) ወይም ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት) ያለብዎ ስለመሆኑ
- ትኩሳት ካለብዎ
- የደም መፍሰስ ችግር ወይም የደም መቅጠን ካለብዎ
- የበሽታ መከላከል አቅምዎ የተዳከመ ከሆነ ወይም የበሽታ መከላከል ስርአትዎ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥር መድሀኒት እየወሰዱ ከሆኑ
- ነፍሰ ጡር ከሆኑ ወይም የማርገዝ እቅድ ካሉዎ
- የሚያጠቡ ከሆነ
- ሌላ የCOVID-19 ክትባት ከወሰዱ
- ከክትባት ጋር በተያያዘ እራስዎን ስተው የነበር ከሆነ

**COMIRNATY የሚሰጠው እንዴት ነው?**
COMIRNATY በመርፌ መልኩ በጡንቻ ላይ ይሰጣል።

[1] COMIRNATY (2023-2024 Formula) የተዘጋጀው ከፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት (ዋናው ሞኖቫለንት/monovalent) እና ከፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent ጋር በተመሳሳይ ዘዴ ነው፣ ነገር ግን የ SARS-CoV-2 የኦሚክሮን (Omicron) ዝርያ XBB.1.5 (ኦሚክሮን XBB.1.5) ስፓይክ ፕሮቲን ያመነጫል።

**COMIRNATY ሊያስከትላቸው የሚችላቸው ስጋቶች ምንድን ናቸው?**
COMIRNATY ከባድ የአለርጂ አፀፋዊ ምላሽ ሊያስከትል የሚችልበት በጣም አነስተኛ ዕድል አለ። ከባድ አለርጂ በዋናነት የሚያጋጥመው አንድ ዶዝ ከተወሰደ በኋላ ካሉት ጥቂት ዲቃዎች ጀምሮ እስከ 1 ሰአት ያክል ነው። በዚህም ምክንያት የክትባት አቅራቢዎ የክትባቱን ሁኔታ ለመቆጣጠር እንዲያስችለው ክትባቱን በወሰዱበት ቦታ እንዲቆዩ ሊጠይቅዎት ይችላል። የከባድ አለርጂ ምልክቶች የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፡

- የመተንፈስ ችግር
- የፊት ወይም ጉሮሮ እብጠት
- የልብ ምት መፍጠን
- ከባድ የሙሉ ሰውነት መንደብደብ
- መደበትና ድካም

ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት) ወይም ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት) በጥቂት COMIRNATYን የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ጨምሮ የ mRNA COVID-19 ክትባቶች በወሰዱ ሰዎች ላይ ተከስቷል። የCOMIRNATY ክትባትን ተከትሎ ማዮካርዲቲስ እና ፔሪካርዲቲስ በብዛት የተከሰቱት እድሜያቸው ከ12 ዓመት እስከ 17 ዓመት በሆኑ ወንዶች ላይ ነው። በእነዚህ አብዛኞቹ ግለሰቦች ላይ ምልክቶቹ መታየት የጀመሩት ክትባቱን በወሰዱ በጥቂት ናት ውስጥ ነው። ይህ የሚያጋጥምበት እድል በጣም ዝቅተኛ ነው። እርስዎ ወይም ልጅዎ ክትባቱን ከወሰዳችሁ በኋላ፣ በተለይም የክትባቱን ዶዝ ከወሰዳችሁ በኋላ ባሉት 2 ሳምንታት ውስጥ የትኛውም የሚከተሉት ምልክቶች ከታዩባችሁ ወዲያውኑ የህክምና ክትትል ያድርጉ፥

- የደረት ህመም
- ትንፋሽ ማጠር
- የፈጣን አተነፋፈስ፣ የልብ መርገብገብ ወይም መውጋት ስሜት

ከCOMIRNATY ወይም የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ጋር ሪፖርት የተደረጉት የጎንዮሽ ጉዳቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፥

- ከባድ አለርጂ
- እንደ መንደብደብ፣ ማሳከክ፣ ሽፍታ ወይም የፊት እብጠት የመሳሰሉ ከባድ ያልሆኑ አለርጂዎች
- ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት)
- ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት)
- ክትባቱ የሚሰጥበት የሰውነት ክፍል አካባቢ የሚፈጠሩ አሉታዊ ምላሾች፥ ህመም፣ መቆጣት፣ መቅላት፣ የክንድ ህመም
- ጠቅላላ አሉታዊ ምላሾች፡ ድካም፣ ራስ ምታት፣ የጡንቻ ህመም፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ የመገጣጠሚያ ህመም፣ ትኩሳት፣ ማቅለሽለሽና፣ ጥሩ ስሜት ያለመሰማት፣ የብሽሽት እብጠት (lymphadenopathy)፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ፣ ተቅማጥ፣ ማስመለስ፣ መፍዘዝ
- ከክትባቱ ጋር በተያያዘ እራስዎን ስተው ያውቁ ከሆነ

የCOMIRNATY ክትባት የሚያስከትላቸው የጎኒዮሽ ውጤቶች እነዚህ ብቻ ላይሆኑ ይችላሉ። እርስዎን የተመለከቱ የጎንዮሽ ጉዳቶችን አስመልክቶ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ይጠይቁ።

የክትባቱን የጎኒዮሽ ውጤቶች ለFDA/CDC የክትባት አሉታዊ ክስተት ሪፖርት ማቅረቢያ ሲስተም (VAERS) ሪፖርት ያድርጉ። የVAERS የነጻ ጥሪ መስመር 1-800-822-7967 ነው ወይም በኦንላይን በ https://vaers.hhs.gov/reportevent.html ሪፖርት ያድርጉ።

በተጨማሪም፣ የጎኒዮሽ ጉዳቶችን ለ Pfizer Inc. በስልክ ቁጥር 1-800-438-1985 ወይም በ www.pfizersafetyreporting.com ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።

**ነፍሰ ጡር ቢሆኑ ወይም እያጠቢ ቢሆንስ ምን ይሆናል?**
ነፍሰ ጡር ከሆኑ ወይም የሚያጠቡ ከሆነ ስለ አማራጮችዎ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይወያዩ።

**የCOMIRNATY ግብአቶች ምንድን ናቸው?**

COMIRNATY የመሚከተሉትን ግብአቶች ይይዛል፡

- ሜሴንጀር ሪቦኒውሴሊክ አሲድ (mRNA)፣
- ሊፒዶች ((4-ሀይድሮክሲቡቲል)አዛንዲል)bis(hexane-6,1-diyl)bis(2-hexyldecanoate)፣ 2 [(ፖሊትሊን ግሎኮል)-2000]-N,N-ዳይትሬድሲላሴታሚድ፣ 1,2-ዲስትሮይልl-sn-ግሊሴሮ-3- ፎስፎኮሊን እና ኮሌስትሮል)፣
- ትሮሜታሚን
- ትሮሜታሚን ሀይድሮክሎራይድ
- እና ስኳር

COMIRNATY ምንም አይነት ሳይበላሽ ማቆያ ነገር አይጠቀምም።

ይህ መረጃ ለተቀባዮችና ለተንከባካቢዎች የቀረበ ሲሆን ወቅታዊ ተደርጎ ሊሆን ይችላል። ለተቀባዮች እና ተንከባካቢዎች ሀቅርብ ጊዜ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ፣ እባክዎን https://dailymed.nlm.nih.gov/dailymed/ የሚለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ።

ምንም አይነት ጥያቄ ካለዎት፣ እባክዎ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይነጋገሩ ወይም www.COMIRNATY.com የሚለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር 1-877-VAX-CO19 (1-877-829-2619) ይደውሉ።

የተመረተው ለ፥
BioNTech Manufacturing GmbH
An der Goldgrube 12
55131 Mainz, Germany

አምራች፥
Pfizer Inc., New York, NY 10001

LAB-1587-1.0
የዩኤስ መንግስት የፍቃድ ቁጥር፥ 2229

የተሻሻለበት ቀን፥ 09/2023